የወ/መ/ቁጥር 159364

የልደታ ምድብ 5 ኛ ወንጀል ችሎት

ሰኔ 09 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ አቶ ቢንያም ተሾመ ወ/ሃዋርያት - ከጠበቃ መስፍን ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ጥቅምት 20 ቀን 2002 ዓ.ም በተሻፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 658(ሀ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በአመልካች በወ/ሮ ሰላም ወርቁ እና በተከሳሽ በራሱ መካከል በነበረው ለልጅ የቀለብ ተቆራጭ ያድርግልኝ አቤቱታ መነሻ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መጋቢት 07 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ለልጁ በየወሩ የቀለብ ሂሳብ ብር 1100(አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር) ከጥር ወር 2001 ዓ.ም ጀምሮ ተቆራጭ እንዲያደርግ ታዞ ያለበቂ ምክንያት በሕጉ መሰረት ሊሰጥ የሚገባውን ቀለብ ለባለመብቷ ሳይሰጥ እስከ ግንቦት ወር 2001 ዓ.ም በመቆየቱ በፈፀመው ቀለብ መስጠት ግዴታን አለመወጣት ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሶትና ተነቦለት ከተረዳው በኋላ ክሱን ሳይቃወም፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሁለት ምስክሮችንና መጋቢት 07 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰጠን የፍ/ቤት ውሳኔ አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱ መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ብይን አንደኛ ምስክር(የግል ተበዳይ) የሆኑት ተከሳሹ ከጥር 2001 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት ወይም እስከ ሰኔ ያለውን የስድስት ወር የቀለብ ክፍያ ፍ/ቤቱ የወሰነውን ብር 1100(አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር) በባንክ አላስገባም፤ ቅዳሜ፤ ቅዳሜ ልጁን ሊወስድ ሲመጣ እንዲያስገባ ነግሬዋለሁ፤ከዚህ በፊ እራሱ ይጠቀምበት የነበረ የእኔ አካውንት አለ ያውቃል፤ የፍትሐብሔር ዳኛውም አስቸግሯል ከፈለግሽ በወንጀል ክሰሺው ስላለኝ ነው የመጣሁት በማለት የመሰከረች ሲሆን፤ ሁለተኛ ምስክር ተከሳሽ የስድስት ወይም የሰባት ወር ውዝፍ የቀለብ ሂሳብ አልከፈለም፤ ልጁን ሊወስድ አንድ ቅዳሜ በመጣ ጊዜ የግል ተበዳይን ከእኔ አምስት ሳንቲም አታገኝም ሲላት ሰምቼአለሁ፤ ከግል ተበዳይ ጋር ፍ/ቤት አብረን ሄደን ዳኛው በወንጀል ክሰሺው ብሏታል፤ የግል ተበዳይ ገንዘቡን መቀበያ በአቢሲኒያ ባንክ አዲስ አካውንት እንዳወጣችም ነግራኛለች ብለዋል። በዚህም መሰረት ዐ/ሕግ ክሱን በማስረጃ ያረጋገጠ ስለሆነ ተከሳሽ በተከሰሰበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 658(ሀ) ስር እንዲከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዟልኛ፤

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብሎ በመጀመሪያ ደረጃ ተከሳሹ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(3) መሰረት የሚሰጠው ቃል፤ ሌላው የግል ተበዳይና ተከሳሽ ይከራከሩበት የነበረው ፍቺውን የሚመለከተው የፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር 127532 የሚያስረዳውም መጋቢት 07 ቀን 2001 ዓ.ም በችሎት ትዕዛዝ የተሰጠው ለግል ተበዳይ እንዲከፈል መሆኑን እንጂ ለባንክ እንዲያስገባ ትዕዛዝ ያልሰጠ መሆኑን፤ በየችሎቱ የቀለብ ጉዳየን አስመልክቶ በግል ተበዳይ ጥያቄ ቀርቦ የማያውቅ መሆኑንና ዳኛውም የቀለብ ጥያቄውን በተመለከተ የግል ተበዳይ በወንጀል እንዲከሱ ትዕዛዝ ያልሰጠ መሆኑን ነው። በሌላ በኩል ከዳሸን ባንክ ቦሌ ኤርፖርት አካባቢ ቅርንጫፍ የቀረበ ሰነድ ሲሆን የሚያስረዳውም የግል ተበዳይ በዚህ ችሎት ሲመሰክሩ በባንክ እንዲያስገባ ትዕዛዝ የተሰጠ አስመስለው፤ የባንክ አካውንቱንም ተከሳሽ በትዳር ጊዜ ጀምሮ የሚያውቀው ነው ብለው የመሰከሩ ሁነው ሳለ ነገር ግን ሰነዱ የግል ተበዳይ ሂሳብ የከፈቱበት ቀን ሰኔ 01 ቀን 2001 ዓ.ም መሆኑንና ተከሳሽ ከሐምሌ 06 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የቀለብ ግዴታውን የተወጣ መሆኑን አስከ መጨረሻው ድረስ የቀረ የቀለብ ክፍያ ያለመኖሩንና የግል ተበዳይ በችሎት ቀርበው የሰጡትን የምስክርነት ቃል በሙሉ የሚያስተባብል ነው በማለት አስመዝግበው ያጠቃለሉ ሲሆን ተከሳሽም በጠየቁት መሰረት ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስና ማስረጃ አስተባብሏል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን ተከሳሽ ከግል ተበዳይ ጋር የነበረው ትዳር በተመለከተ በፍቺ እንዲፈርስ በግል ተበዳይ በኩል ቀርቦ ክርክር እየተካሄደ እያለ በዚህ መካከል መጋቢት 07 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን ተከሳሽ ከጥር ወር 2001 ዓ.ም ጀምሮ ለልጁ በየወሩ የቀለብ ብር 1100(አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር) ተቆራጭ እንዲያደርግ ታዟል፤ የቀለብ ተቆራጭ በየወሩ መጨረሻ ከ25-30 ባሉት ቀናት ውስጥ ለአመልካች እንዲከፍል ታዟል የሚል ነው። ከዚህ በኃላ ተከሳሽ እስከ ሐምሌ 06 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ገንዘቡን ያልከፈለ መሆኑን ከራሱ ከተከሳሽም የተረጋገጠና ማስረጃም የቀረበበት ጉዳይ ነው። ነገር ግን ተከሳሽ ይህን ገንዘብ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ከሰጠበት ከመጋቢት 07 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 06 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ገንዘቡን(የቀለብ ክፍያውን) ያልከፈለው በበቂ ምክንያት ነው ወይስ ያለበቂ ምክንያት ነው የሚለው ወሳኝ ነጥብ ነው። ተከሳሽ እንደሚከራከረው ገንዘቡን ለግል ተበዳይ በእጇ ለመክፈል ሚያዝያ 03 ቀን 2001 ዓ.ም ሄጀ ደረሰኝ ፈርሚልኝ ስላት የባንክ ሂሳቤን በጠበቃህ በኩል ይነገርሀል በማለት ለመቀበል ፍቃደኛ ሳትሆን ቀርታለች ብሏል። ይሁን እንጂ የግል ተበዳይ ይህን ድርጊት ስለመፈፀሟ ወይም ገንዘቡን ለመቀበል እምቢተኛ መሆኗን የሚያስረዳ ከራሱ የተለየ ተጨማሪ ማስረጃ አቅርቦ አላስረዳም። ከመጋቢት 07 ቀን 2001 ዓ.ም ቀጥሎ በነበሩት የፍ/ቤቱ ቀጠሮዎች ተከሳሹ በተከታታይ ሲቀርብ ስለነበር ገንዘቡን በችሎት አቅርቦ የግል ተበዳይ ወይም ጠበቃቸው ክፍያው የሚፈፀምበትን ሁኔታ ማመቻቸት ሲችሉ ይህን አልፈፀሙም። ምክንያቱም ዞሮ ዞሮ ሕፃኑ የጋራ ልጃቸው ስለሆነ የግል ተበዳይ እንኳ እምቢተኛ ብትሆን ለልጁ ጥቅም ሲባል ይህን መፈፀም ነበረበት። ይህም የሚያስረዳው ተከሳሽ በወቅቱ የቀለብ ክፍያውን ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን ሳይሆን በተቃራኒው ነው። ከዚህ ሌላ ተከሳሽ ገንዘቡን በባንክ ሂሳብ ስከፍት ነው የምትከፍለው ስለማለቷ ገለልተኛ የሆነ ከራሱ ሌላ ማስረጃ ወይም ምስክር አላቀረበም። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከሳሽ ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስና ማስረጃ ያላስተባበለ ስለሆነ በወንጀል ሕግ

አንቀፅ 658(ሀ) ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ ፍ/ቤቱ ደረጃውን አቤቱታው ሲወስን በግሉ ልጅ ላይ ስለሆነ ድርጊቱን
የፈፀመው ይህ ከግንዛቤ እንዲገባና በዚሁ መሰረት ተገቢ ነው የተባለው
ቅጣት እንዲወሰን በማለት አመለከቱ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 32 ዓመት ነው፤ ሥራዬ የግል ሥራ ሲሆን በወር ከብር
2000.00(ሁለት ሺህ) እስከ 3000.00(ሦስት ሺህ ብር) ድረስ ነው፤
የትምህርት ደረጃዬ 12 ኛ ክፍል ነው፤ እናቴን እረዳለሁ፤ ከአሁን በፊት
በሌላ የወንጀል ድርጊት ተቀጥቼ አላውቅም፤ ገንዘቡ በወቅቱ
ያልተከፈለበት ምክንያት የግል ተበዳይ በወቅቱ የባንክ ሂሳብ
ባለመክፈቷ ነው፤ ከዚያም በኋላ ግን እስከ አሁን ድረስ ምንም ሳላጓድል
እየከፈልኩ ነው ያለሁት በማለት አመልክቷል።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ 1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሹ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 658(ሀ) /የቀለብ መስጠት ግዴታን አለመፈፀም ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው የስድስት ወር የቀለብ ክፍያን ባለመክፈል በመሆኑና ይህ ጊዜም ከፍተኛ ነው የማይባል ስለሆነ፤ በወቅቱ ድርጊቱም የተፈፀመው በግል ተበዳይና በተከሳሽ መካከል የፍቺ ጥያቄ ቀርቦ ገንዘብ ለመቀባል ቀርቶ እንዲሁ ለመነጋገር የማይችሉበት ምክንያት የነበረ መሆኑ ደረጃውን ከባድ የማያደርግ ቢሆንም ድርጊቱ የተፈፀመው በትዳር ጓደኛው በነበረችውና ዞሮ ዞሮ ለልጁ የሚውልን ቀለብ ባለመክፈል የተፈፀመ ስለሆነ የወንጀል ደረጃው መካከለኛ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት ቅጣቱን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 658(ሀ) የሚያስቀጣው በመቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ያስቀጣል ተብሎ የተደነገገ ስለሆነ ከሁለቱ የቅጣት አይነቶች ፍ/ቤቱ በቅድሚያ አንድን መምረጥ ስላለበት ተከሳሽ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ከስድስት ወር በኋላ ቢሆንም በአንድ ጊዜ የከፈለ በመሆኑ፤ ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ገንዘቡን ሳያቋርጥ እየከፈለ ስለሆነ፤ ይህ ጥፋትም የመጀመሪያው ስለሆነና የአሁንና በዚህ ጥፋት መሰረት ዝቅተኛ የሆነውን የቅጣት አይነት መቅጣቱ ተገቢ ነው ብሎ ፍ/ቤቱ ስላመነ በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል።

ፍ/ቤቱ ተከሳሽን በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ከወሰነ ደግሞ በመመሪያው አንቀፅ 13(10) መሰረት የሚወሰን ሲሆን፤ በዚህም መሰረት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 658(ሀ) የገንዘብ መቀጮው ከብር አስር እስከ አስር ሺህ ስለሆነና የወንጀል ደረጃው መካከለኛ በመሆኑ መነሻ ቅጣቱ ከጣሪያው ብር አስር ሺህ አንድ ሦስተኛ ዝቅ ብሎ ተሰልቶ ከሚገኘው ውጤት ጣሪያ ሳይበልጥ ይወሰናል። የብር አስር ሺህ አንድ ሦስተኛ ውጤት ብር 6667.00(ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ሰባት ብር) ስለሚሆን ቅጣቱ በብር 3333.00(ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ሰላሳ ሦስት ብር እና በብር 6667.00(ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ሰባት ብር) መካከል ይወሰናል። ፍ/ቤቱም የተከሳሽን የወር ገቢንና ሌሎች የሚረዳቸው ሰዎች መኖርን ከግንዛቤ በማስገባት ቅጣቱ ብር 3500.00(ሦስት ሺህ አምስት መቶ ብር) እንዲሆን ተወስኗል። ይህን መነሻ ቅጣት ይዘን ወደ መመሪያው አባሪ ሁለት ስንሄድ ይህ የብር 3500.00(ሦስት ሺህ አምስት መቶ ብር) የገንዘብ መቀጮ በአባሪ ሁለት እርከን 5 ስር የሚወድቅ በመሆኑ፤ የእርከን 5 ፈቃደ ስልጣን ደግሞ እስከ ብር አምስት ሺህ ብር ድረስ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ከላይ የወሰነውን ብር 3500.(ሦስት ሺህ አምስት መቶ ብር) የሚለውጥበት የተለየ ምክንያት ስላላገኘ ይህንኑ መጠን በቅጣትነት ወስኗል።

በዐ/ሕግ በኩል የቅጣት ማክበጃ ስላልቀረበ፤ በተከሳሽም በኩል በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ስላልቀረበ ፍ/ቤቱ ከላይ የወሰነውን መጠን ብር 3500.00(ሦስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ን ተከሳሽ በመቀጮነት እንዲከፍሉ ወስኗል።

ትዕዛዝ

1 ኛ. ተከሳሽ የቅጣት ገንዘቡን ሲከፍሉ ይለቀቁ።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

4 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።